EthioLion.Com

# ተረግጠህ ተገዛ
# ወይ ክንድህን አንሳ

I am only one,
But still I am one.
I cannot do everything,
But still I can do something.
And because I cannot do everything
I will not refuse to do
The something that I can do.
EDWARD EVERETT HALE




ሰምቶ ፣ ዝም
አይቶ ፣ ዝም !
በሆድ ያለ አይነቅዝም ፣
ሲሉህ አብረኽ አታዝግም፣
እያስተኙኽ ነው በህልም ፡፡

አዎን ማለት መረታት፣
አለመመከት መመታት፣
እንዳሉት አበው በመጻፍት፣

ከጓዶችህ ጋር ሰነባብት፣
ምከር በጋራ በቀናት፣
በህገ አራዊት ሥርዓት፣
ላለመገዛት በህወሀት፣
ክንድህን አንሳ በሰዓታት፣
ጊዜ አትስጣቸው ሳምንታት ፡፡

አሊያ ወይ ለራስህ ነጻነት ስትል ታገል፣
አለበለዝያ እንደወደል አህያ ተረግጠህ ዝምበል፣
አታሳድፍ ወኔያቸውን መንፈሳቸውን አትበክል፣
የጀግኖች አባቶችህን አጽሞች አታበራይ አታንጓልል፣

ቡከን ! ለራስህ አልቅስ በቁምህ እያበላህ ተዝካርክን፣
ከገዳይህ ጋር ፈትፍት የውርደት ፍትፍት ዘካህን፣
ይልቅስ .... ይልቅስ... መክተህ ግደል የማይተውኽን ጠላትክን፣
ተንበርክከህ ከመኖር የውርደት ኑሮ ዘመንክን ፡፡

ይህ ግጥም ለቀድሞ የቅንጅት መሪዎች መታሰቢያ የቀረበ የነበረ ሲሆን፣ አሁን ደግሞ ተስተካክሎ በቅርቡ በወያኔ የፈጠራ ክስ እሥር ቤት ለተውረወሩት ወገኖቻችንና እንዲሁም፣ ከዚህ በፊትም በወያኔ ጉሮኖ ለተወረወሩት ጀግኖች ወንድሞቻችንና፣ እህቶቻችን መታሰቢያ ይሆን ዘንድ የተበረከተ ግጥም፡ነው፡፡

እንግዳ ታደሰ ሚያዝያ 20/ 2001

EthioLion.Com